በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-196340

ቀን፡-29/02/2014ዓ.ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግ ማኅበር - ጠበቃ ነጋ ጌታነህ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን- ነ/ፈጂ ደመቀ ሞልዬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኮንስትራክሽን ሥራ ዉል አፈጻጸም መሰረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረተዉ ክስ ነዉ፡፡በግራ ቀኙ መካከል በቀን 10/05/2008ዓ/ም የመገጭ ግድብ የዉሃ ማማ የመሰረት ምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮ ግንባታ ሥራ ዉል ተደርጓል፡፡የግንባታ ዉሉ ጠቅላላ ዋጋ ተጨማሪ እሴት ታክስ(ተ.እ.ታ) ጨምሮ ብር 57,500,9200.00 ነዉ፡፡ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች የዉሉ አካል እንዲሆን ስምምነት ተደርጓል፡፡ተጠሪ ብር 11,500,184.00 ለአመልካች ቅድመ ክፍያ ፈጽሟል፡፡አመልካች ግንባታዉን በ360 ቀናት በማጠናቀቅ ለተጠሪ ለማስረከብ ግዴታ ገብቷል፡፡ተጠሪ የግንባታ ሥራ ቦታ ለአመልካች በቀን 29/06/2008ዓ/ም አስረክቧል፡፡

ሆኖም ግንባታዉ የዘገየዉ የግንባታ ሥራዉ በሚከናወንበት ወቅት በሃገሪቱ በተለይ በአማራ ክልል ጎንደርና አካባቢ በተነሳዉ የሕዝብ አመጽ በተፈጠረ ሁከት መንግስት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያወጀበት ጊዜ ስለነበር ከቀን 30/12/2008ዓ/ም እስከ ቀን 14/02/2009ዓ/ም ለ79 ቀናት የግንባታ ሥራዉ ተቋርጧል፡፡ይህም

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1793 መሰረት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ በጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች ቁጥር 18.6 መሰረት ከአመልካች ቁጥጥር ዉጭ ነዉ ተብሎ የሚወሰድ ነዉ፡፡ይህንን ምክንያት በመጥቀስ አመልካች በቀን 04/12/2008ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ የ102 ቀናት የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ለተጠሪ ቢያቀርብም ተጠሪ በዉል ጠቅላላ ሁኔታዎች አንቀጽ 18.6፣73(1/ረ እና ሸ) ከዉልና ከሕግ የመነጨ ምክንያት በመጥቀስ ለአመልካች ጊዜ ይራዘምልኝ ጥያቄ በ21 ቀን ዉስጥ ምላሽ ስላልሰጠ የማስረከቢያ ጊዜዉ በዉል ተለይቶ እንዳይሰን በማድረጉ የማስረከቢያ ጊዜዉ በአእምሮ ግምት በቂ የሆናል ተብሎ ስለሚወሰን(time at large) በዉሉ የተመለከተዉ የማስረከቢያ ጊዜ የማይፀና ሆኗል፡፡ አመልካች ለግንባታ ሥራዉ መዘግየት ተጠያቂነት ሳይኖርበት ተጠሪ ዉሉን በሕገ-ወጥ መንገድ አቋርጧል፡፡የተፈጠረዉ ከአቅም በላይ ምክንያት ከ60 ቀናት በላይ ስለቆየ በዉሉ ጠቅላላ ሁኔታዎች አንቀጽ 21.3/መ መሰረት አመልካች ዉሉን መቋረጥ መብት ቢኖረዉም አላቋረጠም፡፡ይልቁንም ግንባታዉ በተፈጠረዉ የጸጥታ ችግር ምክንያት ተቋርጦ ከቆየ በኂላ አመልካች ሥራዉን እንዲቀጥል አማካሪዉ በቀን 01/04/2009ዓ/ም ጽፎ ለአመልካች በግልባጭ አሳዉቋል፡፡ አመልካች ሥራዉን በቀን 24/12/ 2009ዓ/ም በቁጥር የኢኮስኮ/8390/09 በጻፈዉ ደብዳቤ አመልካች ሥራዉን በታቀደዉ የማስረከቢያ ጊዜ በቀን 20/07/2009ዓ/ም አላጠናቀቀም በሚል ቀኑን ወደኂላ በማድረግ ዉሉን አቋርጧል፡፡

ስለሆነም አመልካች ለዉሉ መዘግየት ተጠያቂነት ሳይኖርበት ተጠሪ ዉሉን በሕገ-ወጥ መንገድ አቋርጧል ተብሎ እንዲወሰን፡፡ ዉሉ በተቋረጠበት ጊዜ አመልካች ከሚቆፈረቱ 64 ጉድጓዶች ዉስጥ 21 የቆፈረ በመሆኑ አመልካች ለሰራዉ ሥራ ብር 12,794,644.30 ሊከፈለዉ ስለሚገባ ከዚህ ላይ በቅድመ ክፍያ መልክ የከፈለዉ ብር 11,500,184.00 ተቀንሶ የሚቀረዉን ብር 1,294,460.30 ዉሉ ሲቋረጥ መክፈል ሲገባዉ ስላልከፈለ ከቀን 22/04/2008ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል እንዲወሰንበት፡፡ዉሉ የተቋረጠዉ አመልካች ተጠያቂ በሚሆንበት ምክንያት ባለመሆኑ ተጠሪ ከአመልካች ተከፋይ ሂሳብ ላይ በቅጣት መልክ የቀነሰዉን ብር 5,750,000.00 ለአመልካች ተመላሽ እንዲያደርግ እንዲወሰንበት፡፡አመልካች ለግንባታዉ መዘግየት ተጠያቂ ነዉ የሚባል ከሆነ በዉሉ አንቀጽ 87.1 መሰረት ቅጣት የሚቀነሰዉ ላልተሰሩ ሥራዎች መጠን ብቻ ነዉ ተብሎ እንዲወሰን፡፡ተጠሪ ዉሉን ሲያቋርጥ የአመልካች የግንባታ መሳሪያዎች አግቶ በመያዝ አመልካች በንብረቱ እንዳይገለገል በማድረጉ አመልካች ከማሽኖቹ ያጣዉን ገቢ እስከ ቀን 23/10/2010 ዓ/ም ድረስ በተወሰደ የዋጋ ጥናት የተጣራዉን ከተ.እ.ታ በፊት ብር 59,136,000.00 እንዲከፍል እንዲወሰንበት፡፡ ተጠሪ ዉሉን በሕገ-ወጥ መንገድ ሲያቋርጥ ከጊዜ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ተጨማሪ የክፍያ ጥያቄዎች በዉሉ ጠቅላላ ሁኔታዎች አንቀጽ 18.6፣69.1፣74.1/ተ መሰረት ከተ.እ.ታ በፊት ብር 8,1666,798.15 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል እንደወሰንበት፡፡ እንዲሁም ተጠሪ በቅድመ ክፍያ ዋስትና እና በመልካም አፈጻጸም ዋስትና ላይ የማዘዝ ሥልጣን የለዉም እንዲባልና ለአመልካች እንዲለቅ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠዉ መልስ አመልካች በክሱ የተጠቀሰዉን የግንባታ ሥራ በብር 57,500,920.00 ለመሥራት ከተጠሪ ጋር ዉል ተፈራርሟል፡፡አመልካች በዉሉ መሰረት ቅድመ ክፍያ ብር 11,500,184

ከተጠሪ ላይ ተቀብሏል፡፡አመልካች በዉሉ መሰረት አመልካች ቅድሚያ ክፍያ በተፈጸመለት በ20 ቀናት ዉስጥ ሥራዉን ጀምሮ በ360 ቀናት ግንባታዉን አጠናቆ የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡ለግንባታ ሥራዉ የተጓተተበት ምክንያት አመልካች ባለዉ የፀጥታ ችግር ሳይሆን የአመልካች የማሽን ብልሽት እና ለፕሮጀክቱ ሥራ የሚሆን በቂ የሰዉ ኃይል እና ግብአት ባለመቅረቡ ነዉ፡፡ይሁን እንጂ ድጋሚ ጨረታ ማዉጣት የበለጠ የግድብ ሥራዉ ጊዜ ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል በሚል አመልካች ያሉበትን የአቅም እና የተለያዩ ችግሮች በአስቸኳይ እንዲያርም መግባባት ላይ በመድረስ ላቀረበዉ የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ በቀን 08/05/2009ዓ/ም የ33 ቀናት ተጨማሪ ጊዜ ተጠሪ ለአመልካች ሠጥቷል፡፡አመልካች የፀጥታ ችግር ስለመኖሩና ይህም ሥራዉን እንዳይሰራ ፍፁም እክል የሆነበት መሆኑን በማስረጃ አላስረዳም፡፡የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የግንባታ ሥራዉ በሚሰራብት አካባቢ በተፈጠረ የፀጥታ ችግር ምክንያት የታወጀ አይደለም፡፡ስለሆነም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1792 መሰረት ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ሊባል የሚችል ካለመሆኑም በተጨማሪ የግንባታ ሥራዉን ሊያስተጓጉል የሚችል የፀጥታ ችግር ባለመኖሩ አመልካች በወቅቱ ሥራዉን ሲሰራ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ግንባታዉን እንዲያጠናቅቅ በተደጋጋሚ ተጠሪ ለአመልካች ማስጠንቀቂያ የሰጠ ቢሆንም አመልካች ችግሩን ቀርፎ ግንባታዉን ማጠናቀቅ ባለመቻሉ ከጊዜና ከገንዘብ አንጻር በመንግስት ላይ ከፍተኛ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት ተጠሪ ዉሉን መቋረጡን ለአመልካች በጽሁፍ አሳዉቋል፡፡

አመልካች በቀን 04/12/2008ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ለወደፊት የጊዜ ማራዘሚያ እንደሚጠይቅ ገለጸ እንጂ በዚህ ቀኝ የጊዜ ማራዘሚያ አልጠየቀም፡፡የጊዜ ማራዘሚያ በቀን 09/03/2009ዓ/ም እና በቀን 03/04/2009ዓ/ም በተጻፉ ደብዳቤዎች ጠይቆ በአምስት ቀን ዉስጥ ማለትም በቀን 14/03/2009ዓ/ም መልስ በመስጠት የሥራ መርሀግብር አዉጥቶ ተጨማሪ ማሽነሪና የሰዉ ኃይል አስገብቶ በተጨማሪ 33 ቀናት ዉስጥ እንዲያጠናቅቅ ተጨማሪ ጊዜ ስለተሰጠዉ በ21 ቀን ዉስጥ ላቀረበዉ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ተጠሪ መልስ እንዳልሰጠዉ አድርጎ ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡አመልካችም ይህንን መሰረት በማድረግ ሥራዉን እስከ ቀን 16/08/2009ዓ/ም ድረስ ለማጠናቀቅ በሚያስችለዉ መልኩ የሥራ መርሀ ግብር አዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡የ33 ቀናት ጊዜ ማራዘሚያ ስለተሰጠዉ ተጠሪ ለጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ መልስ ሳይሠጥ ዉሉን እንዳቋረጠ አድርጎ ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይኘት የለዉም፡፡በአጠቃላይ አመልካች የገነባዉ 21 ምሶሰዎች ሲሆኑ ይህም በዉሉ መሰረት ስለመገንባቱ ተሞክሮ አለመረጋገጡ እንደተጠበቀ ሆኖ አፈጻጸሙ ከ1/3ኛ ያነሰ ነዉ፡፡ይህም የአቅም ችግር እንዳለበት ስለሚያሳይ ተጨማሪ 360 ቀናት ቢጨመርለትም ቀሪዉን ሥራ ማጠናቀቅ አይችልም፡፡ስለሆነም ዉሉ የተቋረጠዉ በአግባቡ ነዉ፡፡ተጠሪ ዉሉን ከመቋረጡ በፊት ለተጠሪ የ60 ቀናት ማስጠንቀቂያ እንዲሰጥ ዉሉ ተጠሪን አያስገድደዉም፡፡በዉሉ አንቀጽ 21.2 ላይ ተጠሪ ለአመልካች የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠዉ በፈቃጅ መልክ የተቀመጠ ነዉ፡፡በዚህ መሰረት ማስጠንቀቂያ መስጠት አስፈላጊ የሚሆነዉ በዉሉ አንቀጽ 21.2/ሀ መሰረት ተጠሪ ዉሉን በራሱ አነሳሽነትና ምክንያት የሚያቋርጥ ሲሆን ነዉ፡፡ ግንባታዉን ማጠናቀቂያ ጊዜ በዉሉ በግልጽ ስለተመለከተ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1775 መሰረት ተጠሪ ዉሉን ከማቋረጡ በፊት ለአመልካች ማስጠንቀቂያ ለመስጠት አይገደድም፡፡

አመልካች የ21 ጉድጓዶች ግንባታ ስለፈጸምኩ ብር 1,294,460.03 ይከፈለኝ በማለት የጠየቀ ቢሆንም በዉሉ መሰረት ግንባታ መፈጸሙንና ለታለመለት ዓላማ የሚዉል መሆኑን አስመርምሮ ለተጠሪ ያላስረከበ በመሆኑና በዉሉ አንቀጽ 59.3 መሰረት በአማካሪ መሀንዲሱ አስመርምሮ ይሕንን የሚያሳይ በማስረጃ ባለማቅረቡ ይህንን ገንዘብ ተጠሪ ልከፍል አይገባም፡፡ተጠሪ ከአመልካች ክፍያ ላይ ብር 5,750,000.00 በቅጣት መልክ ቀንሶ ያስቀረዉ በዉሉ አንቀጽ 5 መሰረት አመልካች በዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ ግንባታዉን ባለማጠናቀቁ ምክንያት ግንባታዉ ለዘገየበት ጊዜ በዉሉ አንቀጽ 27 መሰረት የበሰለ ጉዳት ኪሳራ(liquidated damage) በየቀኑ 0.1% የዉሉ ዋጋ 10% እስከሚሆን ድረስ ከተከፋይ ሂሳቡ ላይ ቆርጦ ለማስቀረት ዉሉ በሚሰጠዉ መብት መሰረት የተፈጸመ በመሆኑ አለአግባብ ተቀንሶብኛል ሲል ያቀረበዉ ጥያቄ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡አመልካች ግዴታዉን ሳይወጣ ሲቀር በዉሉ አንቀጽ 58 መሰረት ያስያዘዉ ዋስትና እንዲከፈለዉ ተጠሪ ዋስትናዉን ለሰጠዉ ባንክ ጥያቄ አቅርቦ ገንዘቡን የመዉረስ መብት ስላለዉ ተጠሪ አንደዋና ተቋረጭ ለፕሮጀክቱ ባለበት የግንባታ ሥራዉ ለዘገየበት በየቀኑ ብር 4,927,939.79 እየታሰበ ግንባታዉ ለዘገየባቸዉ ቀናት  በቅጣት መልክ እንዲከፍል አመልካች ምክንያት ስለሆነና ተጠሪ ክፍያ እንዲፈጸምለት ለባንክ ደብዳቤ ስለጻፈ አመልካች ከዋስትና ጋር በተያያዘ ያቀረበዉ ጥያቄ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ አመልካች ከጊዜ ጋር ተያያዥነት ላላቸዉ ተጨማሪ ወጪ ተዳሪጌያለሁ ብሎ በዉሉ ጠቅላላ ሁኔታዎች አንቀጽ 18.6፣69.1 እና 74 መሰረት የሥራ ዉሉ የተቋረጠዉ ከአቅም በላይ ሁኔታ ወይም ሥራዉን ለማስቀጠል የማያስችል ሁኔታ ገጥሞ አሠሪዉ ወይም ተጠሪ የሥራ ዉሉን ያቋረጠ እንደሆነ በመሆና በተያዘዉ ጉዳይ የሥራ ዉሉ የተቋረጠዉ በዚህ አግባብ ካለመሆኑም በተጨማሪ አመልካች ያወጣዉ ወጪ ባለመኖሩና ለወጪ መዳረጉን የሚያሳይ ማስረጃም ያላቀረበ በመሆኑ ከዚህ ጋር አያይዞ ብር 8,166,798.55 እንዲከፈለዉ ያቀረበዉ ጥያቄ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡

እንዲሁም አመልካች ተጠሪ የግንባታ መሳሪያዎችን በሕገ-ወጥ መንገድ አግቶ ስላቆየ ብር 59,136,000.00 እንዲከፈለኝ በማለት የጠየቀዉ ዳኝነት በአጠቃላይ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ መጠን ብር 80,181,307.57 ስላደረገዉ ይህም አመልካች ከዉሉ ዋጋ በላይ ዳኝነት እንደጠየቀ ስለሚያሳይና በዉሉ መሰረት ከዉሉ ጠቅላላ ዋጋ በላይ ካሳ መጠየቅ ስለማይቻል ከዚህ አኳያ የጠየቀዉ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ተያዙብኝ ያላቸዉ ንብረቶች ንብረቶቹ እንደሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ተጠሪ አንዳች የአመልካች ንብረቶች አልያዘም፡፡በጠቅላላ የዉሉ ሁኔታዎች አንቀጽ 23 እና በዉሉ ልዩ ሁኔታ አንቀጽ 64.2 መሰተ ዉሉ በሥራ ተቋራጩ ምክንያት ሲቋረጥ በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ ሁሉም የግንባታ እቃዎች፣መሳሪያዎች እና ጊዜያዊ የግንባታ ሥራዎች የተጠሪ(የአሰሪ) ንብረት እንደሚሆኑ ስለተደነገገ አመልካች ንብረቶቹን የማስመለስም ሆነ አከራይቶ የሚያገኘዉን ጥቅም የመጠየቅ መብት የለዉም፡፡ እንዲሁም አመልካች ማሽኖቹን ወደ ግንባታ ስፍራዉ ያመጣቸዉ ተከራይጦ ይሁን በሌላ መንገድ ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ለቆሙበት ጊዜ የከፈለዉ ክፍያ ስለመኖሩ ያቀረበዉ የኪራይ ክፍያ ሰነድ የለም፡፡ሊከፈለዉ ይገባል እንኳን ቢባል መከፈል ያለበት ዉሉ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ያለዉ ነዉ፡፡ በተጨማሪም ንብረቱን ተከታትሎ በወቅቱ በመሰብሰብ ጉዳት የመቀነስ ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ በራሱ ጥፋት ጥያቄ ሳያቀርብ ለቀረበት ጊዜ ሁሉ ክሱን ከማቅረቡ በፊት ያለዉን

ወደኋላ ሄዶ መጠየቁ ተገቢነት የለዉም፡፡እንዲሁም የጠየቀዉ ካሳ ተመጣጣኝ አይደለም በማለት ክሱ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 220306 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና በግራ ቀኙ የቀረቡለትንና ራሱ ያስቀረበዉን ማስረጃዎች ሰምቶና መርምሮ በቀን 10/02/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ በግራ ቀኙ መካከል ለክሱ መነሻ የሆነዉ የመገጭ ግድብ የዉሃ መቆጣጣሪያ ማማ የመሰረት ምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮ የግንባታ ሥራ ዉል መፈራረማቸዉ፣የግንባተታዉ አጠቃላይ ዋጋ ከተ.እ.ታ ጋር ብር57,500,920.00 እንደሆነ፣ በጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች የተመለከቱትን የዉል ግዴታዎች ለመፈጸመ ግዴታ መግባታቸዉን እና ተጠሪ ለአመልካች ቅድመ ክፍያ ብር 11,500,184.00 መክፈሉ በግራ ቀኙ የታመነ ነዉ፡፡ግራ ቀኙ የተካካዱበትን ጭብጦች በመለየት በግራ ቀኙ መካከል ያለዉን የግንባታ ዉል ተጠሪ ያቋረጠዉ በአግባቡ ነዉ ወይስ አይደለም የሚል ጭብጥ በተመለከተ አመልካች በአካባቢዉ በገጠመዉ የፀጥታ ችግር ምክንያት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሥራ መስራት ባለመቻለ ጊዜ መባከኑን ገልጬ የጊዜ ማራዘሚያ የጠየቅሁ ቢሆንም ተጠሪ መልስ በመንፈግ ከሕግ ዉጭ የሥራ ዉል አቋርጧል በማለት የተከራከረዉን ተጠሪ ዉሉ የተቋረጠዉ በዉሉ የተመለከተዉ ጊዜ ተጠናቆ አመልካች በጠየቀዉ መሰረት ተጨማሪ የ33 ቀን ጊዜ የተራዘመለት ቢሆንም አመልካች የመሳሪያና የሰዉ ኃይል ችግር ስላለበት በራሱ ጉድለት የግንባታዉ ጊዜ በመጓተቱ ምክንያት የሥራ ዉል በሕግ አግባብ የተቋረጠ ነዉ በማለት የተከራከረ ቢሆንም አመልካች አቅርቦ ባሰማቸዉ ምስክሮች ከቀን 19/11/2008ዓ/ም እስከ ህዳር 2009ዓ/ም ድረስ ክፕሮጀክቱ አካባቢ ጎሳን ለይቶ የማጥቃት ሁከትና ብጥብጥ በአካባቢዉ እንደተከሰተ፣በተለይም አመልካችና ሠራተኞች የተጠሪ ሠራተኞች ወደሚገኙበት ወደመገጭ ካምፕ እንዲገቡ በተጠሪ ባለመፈቀዱ ምክንያት ከሳይጡ ወጣ ብሎ በሚገኘዉ ጠዳ ከተማ ላይ አመልካች ለሠራተኞቹ ተከራይቶ በነበረዉ ቦታ ላይ ከፍ ያለ ረብሻ ተፈጥሮ ንብረቱ ተዘርፎ ሠራተኞቹ ለነፍሳቸዉ ሸሽተዉ ማምለጣቸዉን ከዚያም በኋላ ወደሥራ ተመልሰዉ ለመግባት የግርግር ጊዜ እስከሚያልፍ ሲጠበቅ የሥራ ማጠናቀቂያ ጊዜዉ እንዳለፈ ይህም በዉሉም ሆነ በፍትሐ ብሔር ሕግ መሰረት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ አመልካች እንደገጠመዉ አመልካች ከተጠሪ የተሻለ ማስረጃ በማቅረብ አስረድቷል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ላቀረብኩት የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ተጠሪ በ21 ቀን ዉስጥ መልስ አልሰጠኝም በማለት የተከራከረ ቢሆንም አመልካች እ.ኤ.አ በቀን 18/11/2016ዓ/ም ላቀረበዉ ጥያቄ በአማካሪዉ በ5 ቀን ዉስጥ በቀን 23/11/2016 ዓ/ም በተሰጠ መልስ ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጠዉ እንደማይገባና በዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ እንዲያጠናቅቅ ተገልጾ መልስ ተሰጥቶታል፡፡ አመልካች እ.ኤ.አ በቀን 18/11/2016ዓ/ም ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች እንደገጠሙት ገልጾ ለወደፊት የጊዜ ማራዘሚያ እንደሚጠይቅ አሳወቀ እንጂ የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ከዝርዝር መግለጫ ጋር በዉሉ አንቀጽ 73/2 መሰረት አልጠየቀም፡፡አመልካች በአማካሪዉ ዉሳኔ ቅሬታ ካለዉ በጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች(GCC) ወይም (FIDIC) ላይ በተመለከተዉ መሰረት ደረጃዉን ጠብቆ ቅሬታ አላቀረበም፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች እ.ኤ.አ በቀን 12/12/2016 ጽፎ ለ102 ቀናት የጊዜ ማራዘሚያዉ እንዲሰጠዉ በድጋሚ ያቀረበዉን ጥያቄ ተከትሎ ተጠሪ በቀን 08/05/2009ዓ/ም በተያዘ ቃለ ጉባኤ ለአመልካች ጠቸማሪ ጊዜ የሠጠዉ ሲሆን ይህ ጊዜ በቂ አይደለም በማለት ይግባኝ ለሥራና

ከተማ ልማት ሚኒስቴር ካለማቅረቡም በላይ በተሰጠዉ ጊዜ ግንባታዉን ለማከናወን የሥራ መርሀ-ግብር አቅርቦ ወደ ሥራ የገባ ቢሆንም በታቀደዉ ማስረከቢያ ጊዜ ባለማጠናቀቁ ተጠሪ በቀን 15/12/2009ዓ/ም ዉሉን ሊያቋርጥ ችሏል፡፡ከዚህም ፍርድ ቤቱ የተረዳዉ እስከ ቀን 08/05/2009ዓ/ም ድረስ ያለዉን ጊዜ በተመለከተ በግራ ቀኙ በተደረሰዉ ስምምነት መሰረት ለአመልካች የ33 ቀናት ተጨማሪ ጊዜ በመስጠቱ መቋጫ አግኝቷል፡፡ ሆኖም አመልካች የተራዘመለትን ጊዜ ተጠቅሞ እስከ ቀን 16/08/2009ዓ/ም ድረስ ሥራዉን ማጠናቀቅ ይቅርና የዉል ማቋረጫ ደብዳቤ ተጽፎ እስከተሰጠበት ቀን 15/12/2009ዓ/ም ድረስ ከ7 ወር በኋላም ቢሆን ሰርቶ አጠናቅቆ አላስረከበም፡፡ ተጠሪ ለአመልካች ከቀን 08/05/2009ዓ/ም በኋላ ዉሉን ከማቋረጥ በፊት ከተከታታይ 6 ጊዜ ሲያስጠነቅቅ ቆይቶ በቀን 15/12/2009ዓ/ም ዉሉን ያቋረጠዉ አመልካች የግንባታ ሥራዉን በማዘግየቱ ምክንያት በመሆኑ ተጠሪ ዉሉን በአንቀጽ 22(2/ሀ እና መ) መሰት በሕግ አግባብ የተቋረጠ ነዉ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዉሉ 64 የዉሃ መቆጣጠሪያ ማማ የመሰረት ምሰሶ ለመስራት ተስማምቶ የግንባታ ዉሉ ሲቋረጥ አመልካች 21 የዉሃ መቆጣሪያ ማማ የመሰረት ምሰሶ በዉሉ መሰረት መስራቱ በማስረጃ እንደተረጋገጠ ገልጾ ለዚህ ሥራዉ ለቅድመ ክፍያ የተከፈለዉ ተቀንሶ ተ.እ.ታ ጨምሮ ቀሪ ብር 1,294,460.30 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡እንዲሁም ዉሉ በአመልካች ምክንያት ስለተቋረጠ በዉላቸዉ አንቀጽ 19(2 እና 3) እና 27 መሰረት ዉሉ በጊዜዉ ባለመጠናቀቁ ለሚደርሰዉ ጉዳት ተጠሪ ባልተሰራ ሥራ መጠን ልክ በየቀኑ የዉሉን ዋጋ 0.1% የዉሉ ዋጋ 10% እስከሚደርስ ድረስ ለአመልካች ከሚከፈል ክፍያ ላይ የመቀነስ መብት አለዉ፡፡በዚህ መሰረት ተጠሪ ከአመልካች ሊቀንስ የሚገባዉ የጉዳት ካሳ ብር 5,620,645.00 ነዉ በማለት ወስኗል፡፡

እንዲሁም ተጠሪ የግንባታ ዉሉን ሲያቋርጥ የአመልካችን የግንባታ መሳሪያዎች ከቀን 08/12/2009ዓ/ም ጀምሮ ይህ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ በኃይል አግቶ በመያዝ አመልካች በንብረቱ እንዳይገለገል በማድረጉ ተገቢነት የሌለዉ ዉሳኔ በመሆኑ አመልካች በንብረቶቹ ባመለመገልገል ያጣዉን ጥቅም ብር 45,000,000.00 ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል፡፡ሆኖም ከላይ በተመለከተዉ መሰረት ተጠሪ ከአመልካች የሚፈለገዉ እዳ ብር 5,620,645.00 ሲቀነስ ብር 39,379,355 ከተጠሪ የሚጠበቅ ሲሆን አመልካች ለሰራዉ ሥራ ለአመልካች ሊከፈል ይገባል የተባለዉ ብር 1,294,460.30 ሲጨመር በድምሩ ብር 40,673,815.00 ከቀን 05/06/2010ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ሕጋዊ ወለድ ጋር ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍልና የአመልካችን መሳሪያዎች/ማሽነሪዎች እንዲሁም የቅድመ ክፍያ ዋስትና ለአመልካች ሊመለስለት ይገባል በማለት ሌሎች አመልካች የጠየቃቸዉን ዳኝነት ጥያቄዎች ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱም በመ/ቁጥር 187031 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 25/12/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ በግራ ቀኙ መካከል በተፈጸመ ዉል መሰረት ዉሉ በአመልካች ምክንያት በዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ ሳይጠናቀቅ በመቅረቱ ዉሉ የተቋረጠ እንደሆነ ተጠሪ የአመልካችን መሳሪያዎች/ማሽነሪዎች በባለቤትነት ተረክቦ በዉሉ የተጠቀሰዉ ሥራ

አስኪጠናቀቅ እንዲጠቀምባቸዉ መብት ተሰጥቶታል፡፡በዚህ መሰረት ተጠሪ በዉሉ የተሰጠዉ መብት ማሽኖቹን ሥራዉ እስኪያልቅ ለመጠቀም የይዞታ መብት እንጂ የባለቤትነት መብት አልተሰጠዉም በሚል አመልካች ያቀረበዉ መከራከሪያ ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ዉሉ በአመልካች ጥፋት መቋረጡ ተጠሪ የማሽኖቹ ባለቤት እንዲሆን በዉሉ ግራ ቀኙ እንደተስማሙ የምንገነዘበዉ ጉዳይ ቢሆንም የተሰጠዉ ባለቤትነት ግን ከዉሉ አጠቃላይ ዓላማ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ በዉሉ ለተጠቀሰዉ ሥራ ማጠናቀቂያ ሰፊ መብት የሚሰጥ እንጂ በዉሉ የተጠቀሰዉ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚቀጥል አይደለም፡፡ስለሆነም መሳሪያዎቹ/ማሽኖቹ የአመልካች በመሆናቸዉ በዉሉ መሰረት አመልካች ያላጠናቀቀዉን ሥራ ተጠሪ በአመልካች ማሽኖች ተጠቅሞ የማጠናቀቅ እና ካጠናቀቀ በኋላ ማሽኖቹን ለአመልካች ሊመልስ ይገባል በማለት የዉሉን ጠቅላላ ሁኔታ አንቀጽ 23.2፣21፣64.2/ሠ እና 83.3ን ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች በማሽኖች ማግኘት እየቻልኩ ተጠሪ ማሽኖቹን በመያዙ ያጣሁት ነዉ ያለዉን ገቢ ተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮ አመልካች መክፈል ከሚገባዉ ቅጣት ከብር 5,620,645.00 ላይ አመልካች ለሰራዉ ሥራ የሚከፈለዉ ብር 1,294,460.30 ተቀንሶ አመልካች ብር 4,326,184.70 ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡

አመልካች የኮንስትራክሽን ሥራ ዉሉ ሲቋረጥ ተጠሪ የአመልካችን ማሽኖች ባለማስረከቡ ማሽኖቹ ያለሥራ በመቆማቸዉ አመልካች ያጣዉን ገቢ እንዲከፍልና ማሽኖቹን/መሳሪያዎቹን እንዲመልስ አመልካች የጠየቀዉን ዳኝነት በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት የደረሰዉን ጉዳት አረጋግጦ በርትእ ብር 39,375,355.00 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል የወሰነዉ ጉዳዩን ከጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አንቀጽ 21.5፣83.1፣83.2፣83.3 እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1205 አንጻር በመመርመር ተጠሪ ማሽኖቹን የመዉረስ መብት እንደሌለዉ ጭምር በማረጋገጥ ስለሆነ ተገቢነት ያለዉ ነዉ፡፡ሆኖም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ተጠሪ ዉሉ ከተቋረጠ ከ3 ዓመታት በኋላ ማሽኖቹን የመዉረስ መብት አለኝ በማለት አግቶ የያዛቸዉን ጊዜያት አመልካች በንብረቶቹ ሳይገለገል የቆየበትን ጊዜያት ከግምት ዉስጥ ሳያስገባ አመልካች ያጣዉን ጥቅም ተጠሪ ሊከፍል አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በፍርድ ሀተታዉ ላይ ተጠሪ የአመልካችን ንብረቶች መያዝ የሚችለዉ አመልካች ያልጨረሳቸዉን ሥራዎች ለመጨረስ ብቻ ነዉ በማለት የአመልካችን ክርክር የሚያጠናክር ምክንያት ከገለጸ በኋላ ከዚህ አግባብ ዉጭ ተጠሪ ማሽኖቹን ከ3 ዓመት በላይ አግቶ ላቆየበት ጊዜ የታጣ ገቢ ሊከፍል አይገባም ማለቱ ዉሳኔዉ እርስ በእርስ የሚቃረንና ሚዛናዊነት የጎደለዉ ነዉ፡፡የተሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ በአመልካች ንብረት ማብቂያ ለሌለዉ ጊዜ ይዞ እንዲቆይ የሚያደርግና አግቶ ያቆየዉን ጊዜ ከግምት ያላስገባና በአመልካች ላይ የደረሰዉንና እየደረሰ ያለዉን ጉዳት ያላገናዘበ በመሆኑ ሕግንና ሞራልን የሚቃረን ስለሆነ አመልካች ያጣዉን ገቢ ተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነዉ አለአግባብ ስለተሻረ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይጽናልኝ በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ ተጠሪ የግንባታ ሥራ በዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ ባለመጠናቀቁ የቀረዉን ሥራ ሠርቶ እስከሚጨርስ ድረስ የግንባታ ሥራ መሳሪያዎችን እንዲይዙና ሥራዉ ሲጠናቀቅ እንዲመልስ ዉላቸዉ መሰረት ተደርጎ ሲወሰን በዉሉ ላይ ሥራዉን የሚጨርሱበት ጊዜ በዉላቸዉ

ባይቀመጥም ከጠቅላላ ዉል ይዘት መሰረት ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 01/06/2013ዓ/ም የተጻፈ የሚከተለዉን መልስ አቅርቧል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት በነበረዉ ክርክር ተጠሪ ማሽኖቹን ሊያዝ የሚገባበትን ጊዜ በተመለከተ ያደረገዉ ክርክር የለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ማሽኖቹን ማብቂያ ለሌለዉ ጊዜ እንዲጠቀምባቸዉ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበዉ መከራከሪያ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 329/1 መሰረት ተቀባይነት የለዉም፡፡ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በዉሉ ጠቅላላ ሁኔታዎች አንቀጽ 23.2 እና 83.3 እንደዚሁም የዉሉ ልዩ ሁኔታ አንቀጽ 64.2/ሠ ላይ ዉሉ በሥራ ተቋራጭ/አመልካች ጥፋት ከተቋረጠ ተጠሪ የአመልካች ጥፋት ከተቋረጠ ተጠሪ የአመልካችን ማሽኖች አመልካች የጀመረዉ ሥራ እስኪጠናቀቅ ድረስ መጠቀም ይችላል የሚል በመሆኑ ዉሳኔዉ የተጠሪን ከዉል የመነጨ መብት መሰረት ያደረገ ዉሳኔ ነዉ፡፡እንዲሁም በዉሉ አንቀጽ 23.2 በግልጽ እንደተመለከተዉ ዉሉ በአመልካች ምክንያት ከተቋረጠ በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ ማሽኖቹን ተጠሪ የመዉሰድ መብት እንጂ ተጠቅሞ የመመለስ በመሆኑ አመልካች ጀምሮ የነበረዉ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላም ቢሆን ተጠሪ የመመለስ ግዴታ የለበትም፡፡በግራ ቀኙ ዉል ጠቅላላ ሁኔታዎች አንቀጽ 83/3 ላይ ዉሉ በስር ተቋራጩ(አመልካች) ምክንያት የተቋረጠ እንደሆነ አሠሪዉ(ተጠሪ) ንብረቱን ሥራዉ እስኪጠናቀቅ ድረስ ለመጠቀም እንደሚችል ይጠቀሳል፡፡ስለሆነም ተጠሪ ማሽኖቹን የመዉረስ ከዉል የመነጨ መብት እያለዉ ይህንን መብት ባለመቀበል ሥራዉ እስኪጠናቀቅ ድረስ የመጠቀም መብት አለዉ ብሎ መወሰኑ ተጠሪን የሚጎዳ ዉሳኔ በመሆኑ ተጠሪ ለአመልካች የሚከፍለዉ የጉዳት ካሳ የለም ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔም አመልካች እንዳለዉ እርስ በእርሱ የሚጣረስ አይደለም፡፡ዉሉ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ የአመልካች ማሽኖች ተጠሪ የግንባታ ሥራዉን በሚያሰራበት ቦታ ላይ ያሉ ቢሆንም የማሽኖቹ ቁልፍ አመልካች እጅ ስለሚገኙና ተጠሪ ቁልፎቹ እንዲሰጠዉ በተደጋጋሚ ተጠይቆ ባለማስረከቡ ማሽኖቹ ላለፉት ሶስት አመታት ማሽኖቹ በተጠሪ ተይዘዋል ቢልም ተጠሪ ተጠቅሞባቸዉ ስለማያዉቅ እስካሁን ተጠሪ በማሽኖቹ እየተገለገለ እንደሚገኝ አድርገዉ ያቀረበዉ ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡በዚህ ምክንያት በማሽኖቹ አልተጠቀምንም እንጂ ብንጠቀም እንኳን ለአመልካች የምንከፍለዉ ክፍያ አይኖርም፡፡ስለሆነም ተጠሪ ማሽኖቹንን እንዲወርስ ዉሳኔዉ ሊሻሻል ይገባል እንጂ ለአመልካች ካሳ የሚከፈልበት የሕግ መሰረት የለም ተብሎ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ነጥብ ከግምት በማስገባት በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደተመረመረዉም ለግራ ቀኙ ክርክር መነሻ የሆነዉ ተጠሪ አመልካችን የመገጭ ግድብ የዉሃ መቆጣጠሪያ ማማ የመሰረት ምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮ የግንባታ ሥራ ለማሰራት በቀን 10/05/2008 ዓ/ም ወይም እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 19 ቀን 2016 ዓ/ም የተፈራረሙት ዉል ነዉ፡፡የግንባታዉ አጠቃላይ ዋጋ ከተ.እ.ታ ጋር

ብር57,500,920.00 እንደሆነ፣ ግንባታዉን በ360 ቀናት ዉስጥ ለማጠናቀቅና በጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች የተመለከቱትን የዉል ግዴታዎች ለመፈጸም ግዴታ መግባታቸዉ በግራ ቀኙ የታመነ ነዉ፡፡እንዲሁም በዉሉ መሰረት ተጠሪ ለአመልካች ቅድመ ክፍያ ብር 11,500,184.00 በቀን 24/06/2008ዓ/ም መክፈሉ፣አመልካች ቅድመ ክፍያ ከተከፈለዉ ቀን ጀምሮ በ20 ቀን ዉስጥ ግንባታ ለመጀመር የዉል ግዴታ መግባቱን፣አመልካች ግንባታ በሚፈጽምበት አካባቢ በተፈጠረ የጸጥታ ችግር ምክንያት ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠዉ ጠይቆ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ እንደገጠመዉ ተረጋግጦ በተጠሪ የ33 ቀናት ጊዜ ተጨምሮለት ግንባታ መፈጸሚያ ጊዜ ተራዝሞለት አመልካች ወደ ሥራ እንደገባ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ በተራዘመዉ ጊዜ አመልካች የሉበትን የሰዉ ኃይልና የማሽነሪ(ግንባታ የመፈጸም አቅም)ችግር መቅረፍ ባለመቻሉ ተጠሪ በዉልና በሕግ አግባብ ዉሉን መቋረጡ፤ዉሉ በተቋረጠበት ጊዜ በዉሉ መሰረት አመልካች መገንባት ከሚጠበቅበት 64 የዉሃ መቆጣጠሪያ ማማ የመሰረት ምሰሶ ጉድጓድ ዉስጥ 21 ብቻ እንደሰራ በግራ ቀኙ የታመነና በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸዉ፡፡እንዲሁም ዉሉ በሚቋረጥበት ጊዜ ግንባታ በሚፈጸምበት ቦታ የአመልካች ንብረት የሆኑ የግንባታ መሳሪያዎች/ማሽነሪዎች በግንባታ ቦታ በተጠሪ ይዞታ ሥር እንደቀሩም የተረጋገጡ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ግራ ቀኙን ያከራከረዉና የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ ዉሉ ሲቋረጥ በግንባታ ቦታ የነበሩትን የአመልካችን መሣሪያዎች/ማሽኖች ቀሪ የግንባታ ሥራ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ተጠሪ ተጠቅሞባቸዉ ግንባታዉን የማጠናቀቅ መብት አለዉ ተብሎ መወሰኑ እና ግንባታዊ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ለሚኖረዉ ጊዜ አመልካች በማሽኖች ማግኘት እችል የነበረዉንና ያጣሁትን ገቢ ተጠሪ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ጠይቆ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተወሰነለትን ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ዉደቅ በማደረጉ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል ስህተት መኖር አለመኖሩን የሚመለከት ነዉ፡፡

በኮንስትራክሽን ሕግጋትና በልማድ የዳብረዉና ተቀባይነት አግኝቶ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች ወይም የሲቪል ሥራዎች ኮንስትራክሽን ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች (Standard conditions of contract for Construction of civil works) በሚል በሚታወቁ ደንቦች ላይ የሚታወቁ የኮንስትራክሽን ሥራ በዉሉ ላይ ተወስኖ በተቀመጠዉ የግንባታ ሥራ ማጠናቀቂያ ጊዜ ዉስጥ እንዳያልቅ ወይም ግንባታዉ ሳይጠናቀቅ እንዲዘገይ የሚያደርጉ የተለያዩ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን እነዚህም በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ እንደተመለከተዉ በአራት የኃላፊነት ገጽታዎችና ኃላፊነት በሚያስከትሉ ሁኔታዎች(risk) ምንጮች ላይ በመመስረት የሚታወቁ ናቸዉ፡፡እነዚህም አንደኛ ሙሉ በሙሉ አሰሪዉን በሚመለከቱ ምክንያቶች ወይም ሁኔታዎች(employer's risk event) የሚከሰት፣ ሁለተኛዉ ሙሉ በሙሉ ሥራ ተቋራጩን(ንኡስ ተቋራጩን ይጨምራል) በሚመለከቱ ሁኔታዎች (contractor's risk event) የሚከሰት፣ሶስተኛዉ አሰሪዉን፣ ሥራ ተቋራጩንና አማካሪ መሀንዲሱን በሚመለከቱ ሁኔታዎች (concurrent risk event/Common risk) የሚከሰት ሲሆን አራተኛዉ ደግሞ በግንባታ ዉሉ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖችን በማይመለከት እና ከእነዚህ አካላት ቁጥጥር ዉጭ በሆኑ ሁኔታዎች(special risk event) የሚከሰት በሚል የሚገለጹ ናቸዉ፡፡

ግራ ቀኙ በተፈራረሙት ዉል አንቀጽ 23.2 እና በዉሉ ልዩ ሁኔታ አንቀጽ 64.2/ሠ እና አንቀጽ 83.3 ስር ዉሉ የተቋረጠዉ በሥራ ተቋራጩ ጥፋት ከሆነ ሁሉም የግንባታ ቁሶች፣መሳሪያዎች፣ጊዜያዊ የግንባታ ሥራዎች እና የግንባታ ሥራዎች የአሠሪዉ እንደሚሆኑ ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል የዉላቸዉ አካል ባደረጉት የሲቪል ሥራዎች ኮንስትራክሽን ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች (Standard conditions of contract for Construction of civil works)ላይ አንቀጽ 63(1/ሠ) ስር ባለዉ የመጨረሻ ፓራግራፍ ላይ የሥራ ተቋራጭ የዉል ግዴታዉን አለመወጣት (Default of contractor) ወይም በሥራ ተቋራጩ ጥፋት ዉሉ በሚቋረጥበት ጊዜ የሚያስከትለዉን ዉጤት በተመለከተ እንደተደነገገዉ ደግሞ አሠሪዉ ከግንባታ ቦታ ሥራ ተቋራጩን በማሰናበት ለግንባታ ሥራዉ ተብለዉ በግንባታ ቦታዉ ገብተዉ የሚገኙ መሳሪያዎችንና ማሽኖችን (construction plant)፣ ጊዜያዊ ግንባታዎችንና ቁሶችን የግንባታ ሥራዉን ለማጠናቀቅ የመጠቀም መብት እንዳለዉና ተገቢ ነዉ ብሎ ሲወስን ከሥራ ተቋራጩ ለሚፈልገዉ ከዉሉ ለመነጨ የበሰለ እዳ እነዚሁን ንብረቶች በመሸጥ ገንዘቡን ማስመለስ(ለዕዳዉ ማካካሻ ማድረግ) እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በዚህ አግባብ ግራ ቀኙ በተፈራረሙትና በዉሉ ጠቅላላ ሁኔታዎች ላይ የተመለከተዉ ሀሳብ በአንድ በኩል ዉሉ የተቋረጠዉ በሥራ ተቋራጩ ምክንያት(ጥፋት) የተነሳ እንደሆነ በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ ንብረቶች ላይ አሠሪዉ የባለቤትነት መብት እንዲያገኝ በሚያደርግ መልኩ የተቀረጸ ሲሆን በሌላ በኩል በግንባታ ቦታዉ ላይ ባሉት በስራ ተቋራጩ ንብረቶች እና/ወይም በጊዜያዊነት በሥራ ተቋራጩ በተሰሩ ግንባታዎች አሠሪዉ ተገልግሎባቸዉ የቀረዉን ሥራ ያጠናቅቃል በሚል በንብረቶቹ የመገልገል መብት አሰሪዉ እንዲኖረዉ በሚያደርግ መልኩ በሚጣረስ አኳኋን የተደነገገ ነዉ፡፡በአንድ ዉል ላይ ባሉ የዉል ቃላት (Provisions) መካከል በዚህ መልኩ አለመጣጣም ሲኖር በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1732 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተዉን የዉል አተረጓጎም መርሆዎች ተከትሎ በመተርጎም ተፈጻሚነት ያለዉን የዉሉን ሀሳብ መለየት ይገባል፡፡

በፍ/ብሕግ ቁጥር 1734 ስር እንደተደነገገዉ የዉሉ ቃል(the provision of contract)የሚያሻማ በሆነ ጊዜ ተዋዋዮቹ ዉላቸዉን ከመዋዋላቸዉ አስቀድሞ ወይም ከተዋዋሉ በኋላ የነበሩበትን ሁኔታ በማመዛዘን የተዋዋዮቹ ሐሳብ ምን እንደነበር በመፈለግ አሻሚ ለሆነዉ የዉል ቃል ትርጉም መስጠት ይገባል፡፡እንዲሁም በዚሁ ሕግ በቁጥር 1732 ስር ደግሞ ዉሎች የቅንነት፣የመተማመንን ግንኙነት መሰረት በማድረግና በጉዳዮቹ ዉስጥ ያለዉን ልማዳዊ ሥርዓት በመከተል በቅን ልቦና ሊተረጎሙ እንደሚገባም ተመልክቷል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገዉ ዉል ጉዳይ(object) በዉሉ የተመለከተዉን ግንባታ በዉሉ በተመለከተዉ አግባብና ጊዜ አመልካች እንዲገነባ ግዴታ የሚጥል ተጠሪ ደግሞ የዉሉን ዋጋ ለአመልካች መክፈልና በዉሉ የዉሉን ጉዳይ ለመፈጸም የተቀመጡ ሌሎች ተግባራትን መወጣት ነዉ፡፡ከጠቅላላ የዉል ሁኔታዎችና ደንቦች፣ በኮንስትራክሽን ሥራ ዘርፍ ከዳበሩ ልማዶች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካች በዚህ ዉል የተመለከተዉን ግዴታዉን በዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ ወይም በስምምነት በተራዘመዉ ጊዜ ሠርቶ በማጠናቀቅ ባያስረክብ ተጠሪ እንደ ዋና ተቋራጭ የሚኖረዉ መብት ግንባታዉ ለዘገየበት ጊዜ በዉሉ አስቀድሞ የተወሰነ ኪሳራ(liquidated damage) ማስከፈል፤ እንደነገሩ ሁኔታ በዉላቸዉና በሕግ አግባብ

ግንባታዉ በጊዜ ባለመጠናቀቁ ምክንያት የሚደርስበትን ሌላ ወጪ ወይም የተረጋገጠ ኪሳራ(actual damage) ማስከፈል እና/ወይም በግንባታ ቦታ ላይ ባሉት የሥራ ተቋራጩ ንብረቶች በመጠቀም ቀሪዉን የግንባታ ሥራ በሌላ ተቋራጭ አሰርቶ ለማጠናቀቅ የሚያስችል በዉል ባገኘዉ መብት መሰረት በራሱ ተግባራዊ ማድረግ ወይም በፍርድ ቤት በአመልካች ላይ እንዲወሰንለት መጠየቅ ነዉ፡፡ ይህም የሚያሳየዉ የዉሉ ጉዳይም ሆነ የሥራ ተቋራጩ የዉል ግዴታ ያለመወጣት ወይም በተቋራጩ መዘግየት ምክንያት ዉሉ በተቋረጠ ጊዜ የሚከተለዉ ዉጤት የተቋራጩን የንብረት ባለቤትነት መብት ወደ አሠሪ ወይም ወደ ዋና ሥራ ተቋራጭ ማስተላለፍ እንዳልሆነ ነዉ፡፡ከዚህ የምንገነዘበዉ ግራ ቀኙ ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተፈራረሙት ዉል ላይም ሆነ የዉላቸዉ አካል ባደረጉት ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች የተደነገገዉን የተስማሙት በአመልካች ጥፋት ዉሉ ሲቋረጥ በግንባታ ቦታ ላይ የነበሩትን ንብረቶች ባለቤትነት መብት ለተጠሪ ለማስተላለፍ በማሰብ ሳይሆን በአመልካች ምክንያት ዉሉ በመቋረጡ ተጠሪ ቀሪዉን ሥራ በራሱ ሰርቶ ለማጠናቀቅ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ አሊያም ሌላ የሥራ ተቋራጭ አስገብቶ ለማጠናቀቅ በሚያደርገዉ እንቅስቃሴ ለሥራዉ አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችን/ማሽኖችን እየፈለገ እና ዋናዉን ግንባታ ለማከናወን የሚያስፈልጉ ጊዜያዊ ግንባታዎችን በመገንባት ተጨማሪ ጊዜ እንዳያባክን እና በአመልካች ጥፋት ለተጨማሪ ወጪ እንዳይዳረግ ለማድረግ፤ እንዲሁም ከሥራ ተቋራጩ የሚፈልገዉ ገንዘብ ካለም እነዚሁኑ የተቋራጩን ንብረቶች እንደመያዣ (lien right) በመጠቀም ማስከፈል እንዲችል መብት ለመስጠት ነዉ፡፡ስለሆነም ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ዉሉ በተቋረጠበት ጊዜ በግንባታ ቦታ የሚገኙትን መሳሪያዎችን/ማሽኖችን ቀሪ ግንባታ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ተጠሪ ይዞ የመገልገል መብት አለዉ በማለት ለዉሉ የሰጠዉ ትርጉም የተዋዋዮችን ሀሳብና የዘርፉን ልማድ ከግምት ያስገባ በመሆኑ ከዚህ አንጻር የተፈጸመ ስህተት አላገኘንም፡፡

እንዲሁም ተጠሪ ይህንን መብት ያገኘዉ ዉሉ አመልካች ኃላፊ በሆነበት ጥፋት(ጉድለት) ምክንያት በመቋረጡ ስለሆነ ተጠሪ ዉሉ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ቀሪዉ ግንባታ እስከሚጠናቀቅ ድረስ አመልካች በማሽኖቹ/በመሳሪያዎቹ ማግኘት የሚችለዉን ገቢ ለመተካት የሚገደድበት የዉልም ሆነ የሕግ መሰረት የለም፡፡ምክንያቱም ከላይ በተመለከተዉ መሰረት ተጠሪ በመሳሪያዎቹ/በማሽኖቹ የመገልገል መብት አለዉ የሚለዉ የዉሉ ጠቅላላ ሁኔታ ዉጤት የሚኖረዉ ተጠሪ በመሳሪያዎቹ/በማሽኖቹ ያለክፍያ መገልገል ሲችል ነዉ፡፡ተጠሪ ለመሳሪያዎቹ ክፍያ እየፈጸመ እንዲገለገል በዉሉ ታስቦ የነበረ ቢሆን ኖሮ መሳሪያዎቹ/ማሽኖቹ በተጠሪ እጅ በሚቆዩበት ጊዜ ተጠሪ ስለሚከፍለዉ ክፍያ አመላካች ድንጋጌ ያስቀምጡ ነበር፡፡በዚህ መልኩ በዉሉ ተጠሪ በመሳሪያዎቹ/በማሽኖቹ በሚገለገልበት ጊዜ ለአመልካች ስለሚከፍለዉ ክፍያ የሚገልጽ የዉል ቃል አለን በማለት ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡በዚህ አግባብ በዉሉ ያልተመለከተዉ ዉሉ በአመልካች ጥፋት በተቋረጠበት ሁኔታ እንዲህ አይነት የሁለቱን ግንኙነት የሚያስቀጥል ሀሳብ በዉሉ ለማኖር ሀሳብ ነበራቸዉ ለማለት የሚያስችል አሳማኝ አመክኒዮ ባለመኖሩና በአመልካች ላይ እንዲህ አይነት ኃላፊነት የመጣበት ዉሉ በሱ ጥፋት በመቋረጡ ምክንያት ስለሆነ ነዉ፡፡

ስለሆነም ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ተጠሪ በዉሉ መሰረት በግንባታ ቦታ በሚገኙት የአመልካች መሳሪያዎች እና/ ወይም ማሽኖች ቀሪዉ ግንባታ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የመገልገል መብት ስላለዉ አመልካች

በመሳሪያዎቹ እና/ ወይም በማሽኖቹ ማግኘት እችል የነበረዉን ገቢ አጣሁኝ በማለት እንዲከፈለዉ የጠየቀዉን ተጠሪ ሊከፍል አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤት ከዚህ አኳያ የወሰነዉን በመሻር የሰጠዉ ዉሳኔ ዉሉንና ሕግን መሰረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር የተፈጸመ ስህተት አላገኘንም፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የእነዚህ መሳሪያዎች እና/ ወይም ማሽኖች ባለቤትነት መብት የአመልካች በመሆኑ ቀሪዉ የግንባታ ሥራ በተጠሪ ምክንያት ወይም በአሰሪዉ ዉሳኔ ወይም በሌላ ምክንያት እንዲቀር ከተደረገ(ከተተወ) አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ላይ ዘርዝሮ ያቀረባቸዉ መሳሪያዎች እና/ ወይም ማሽኖች እንዲመለሱለት ከመጠየቅ ይህ ዉሳኔ የሚያግደዉ አይደለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 187031 ላይ በቀን 25/12/2012ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

1. በዉሳኔዉ መሰረት እንዲፈጽም የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

**አመልካች ፡- ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግ ማኀበር -**

**ተጠሪ ፡-የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን**

ተጠሪ በቀን 01/06/2013 ዓ/ም ጽፎ ያቀረበዉን መስቀለኛ የሰበር አቤቱታ መርምረን የሚከተለዉን ትእዛዝ ሰጥተናል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

የተጠሪ መስቀለኛ አቤቱታ ዉሉ ሲቋረጥ በግንባታ ቦታ የነበሩትን የአመልካችን መሳሪያዎች/ማሽነሪዎች በዉሉ መሰረት እንዲወርስ አለመወሰኑ መሰሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ነዉ፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነዉ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገዉ የኮንስትራክሽን ሥራ ዉል ተጠሪ ቀሪዉን ሥራ በመሳሪያዎቹ/በማሽኖቹ እየተገለገለ እንዲያጠናቅቅ መብት የሚሰጠዉ እንጂ በመሳሪያዎቹ/በማሽኖቹ ላይ የባለቤትን መብት የሚሰጠዉ ባለመሆኑ ከዚህ አንጻር ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በመ/ቁጥር 187031 ላይ በቀን 25/12/2012ዓ/ም እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 220306 በቀን 10/02/2012 ዓ/ም የሰጡት ዉሳኔ ጉድለት ስለሌለባቸዉ አቤቱታዉን ሰርዘናል፡፡